ውጤት	%
አጋማሽ ፈተና	
ተከታታይ ምዘና	
ጠቅላላ	

ኢትዮ-ፓረንትስ ት/ቤቶች አዲስ አበባ (ገርጂ፣ ጉለሌ)ና ሐዋሳ
Fax: +251-116-295034
Gerji (A.A) +251-116-512325
Gullele (A.A) +251-112-593747/48
Hawassa +251-462-22582

የዘጠነኛ ክፍል መለማመጃ ጥያቄ

መመሪያ ፩፦ ከተራ ቁጥር **1** *እስከ* **7** *የቀረቡትን ጥያቄዎች፣ የያዙት ሐሳብ ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ፣ ትክክል ካልሆነ የማመ‹‹ሳሳት›› ባመልክት ጠቅለህ/ጠቅላ።*

1. በአንድ ዓ.ነገር ውስጥ አንድ ግስ ብቻ ካለ ግሱ ማሰሪያ አንቀፅ በመባል ይታወቃል።
2. ፅሁፍን በቃል አጥንቶ ለማቅረብ ዋናና ዝርዝር ነጥቦች የተያያዙበትን ተጠየቅ መረዳት ይገባል።
3. በአንድ ዓ.ነገር ውስጥ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ይገኛሉ።
4. ጅምር ስንኞችን ለማሟላት የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ስንኝ የመጨረሻ ድምፅ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ይገባል።
5. ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ወስዶ የአንዱን ባህሪ ለሌላው በመስጠት የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት አነፃፃሪ ዘይቤ ይባላል።
6. ትልም በተውኔት ውስጥ የሚካሔዱትን ነገሮች በምክንያትና ውጤት ያሳያል።
7. የስራ ደብዳቤ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ እንዲፈፀም ትዕዛዝ ለማስተላለፍ ሊፃፍ ይችላል።

መመሪያ ፪፦ በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን ቃላት በ‹‹ለ›› ስር ከተሰጡት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምደ/ አዛምጂ።

‹‹ሀ››			‹‹ለ››
8.	10.	ለበጠ	(ሀ) ጥቅም
11.	13.	ቋሳ	(ለ) ቂም
14.	16.	ባተሌ	(ሐ) ፍሬ
17.	19.	አላባ	(መ) ልፋት
20.	22.	ፋይዳ	(ሠ) ወፍራም
23.	25.	ደጓሳ	(ረ) ሸፈነ
			(ሰ) ፋታ የሌለው

መመሪያ ፫፦ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደአጠያየቅ ባህርያቸው ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን ምረጪ/ ምረጥ።

1. ‹‹ይዋል ይደር እንጂ የእጁን ያገኛል።›› በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘው ቀጥተኛ ተሳቢ የትኛው ነው?

(ሀ) ይዋል ይደር እንጂ (ሐ) የእጁን

(ለ) እሱ (መ) እነሱ

2. ‹‹እህቱ ከውጭ ስለመጣች ስራ ለቀቀ።›› በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የገባው መስረዋድዳዊ ሀረግ የትኛው ነው?

(ሀ) ስራ (ሐ) ስለመጣች

(ለ) ስለ ለቀቀ (መ) ከውጭ

3. ‹‹አበበ ከሐረር <u>ዶሎ</u> ተመለሰ።›› የተሰመረበት ቃል_____ ነው።

(ሀ) ግስ (ሐ) ተውሳከ ግስ

(ለ) መስተዋድድ (መ) ቅጽል

4. ‹‹ልጆቹ <u>ወደ ቤታቸው ሄዱ</u>።›› የተሰመረበት ሀረግ_____ ነው።

(ሀ) ስማዊ ሀረግ (ሐ) ግሳዊ ገረግ

(ለ) መስተዋድዳዊ ገረግ (መ) ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

5. ‹‹ጅብ እስኪነክስ_____ ምሳሌያዊ አነጋገሩን ለማሟላት የሚገባው ሀረግ የቱ ነው?

(ሀ) ያደፍጥ (ሐ) ይጮብስ

(ለ) ያነክል (መ) በጎን ይሂድ

6. ‹‹የነ ዶሎ ዶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ›› ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር

(ሀ) አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ (ሐ) የቸኮለ አፍሶ ለቀመ

(ለ. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል (መ) ሁሉም መልስ ይሆናል

7. ‹‹አይን አይዶ _____ በጅምር የቀረበውን አባባል ሊያሟላ የሚችለው የቱ ነው?

(ሀ) ልብ ይፈርዳል (ሐ) እጅ ይመክታል

(ለ) ሆድ ይመኛል (መ) ህሊና ያያል

8. ‹‹ክሰር ያለው ቢነግድ አይተርፈውም›› ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጋር አብሮ የሚሄደው የትኛው ነው?

(ሀ) ያልጠረጠረ ተመነጠረ (ሐ) አንኳን ዘንቦባሽ እንዲያውም ጨዛ ነሽ

(ለ) የቸኮለ አፍሶ ለቀመ (መ) ልፋ ያለው በህልሙ ዳውላ ይሸከማል

9. ‹‹አበበ <u>አንደበተ ርቱእ</u> ነው።›› የተሰመረበትን ፈሊጥ በፍቺ ሊተካ የሚችለው የቱ ነው?

(ሀ) ተናግሮ የሚያሳምን ነው። (ሐ) አንደበቱ ቀጥ ብሎ የቆመ ነው።

(ለ) ተናጋሪ ነው። (መ) ንግግሩ ወላዋይ ነው።

10. ‹‹ጥርስ ገባ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

(ሀ) ተጠላ (ሐ) ተፈጨ

(ለ) ታወቀ (መ) ተበላ

11. ጥላ ቢስ

(ሀ) ጥላ የሌለው (ሐ) ሞገስ የሌለው

(ለ) ክብደት የሌለው (መ) ምስል የሌለው

12. ሙጢ አፍ

(ሀ) አፉ ወደፊት ያሞጠሞጠ (ሐ) አፉ ሹል የሆነ

(ለ) አፉ የማያርፍ (መ) ነገረኛ

13. ገመና ከታች

(ሀ) ገንዘብ አቡዳሪ (ሐ) ምስጢር ደባቂ

(ለ) ሽማግሌ ጧሪ (መ) ሰው አክባሪ

14. ወሬው ጠፋ

(ሀ) የወሬው ፕሮግራም አለቀ (ሐ) የሚወደው ወሬ አልገኝ አለ

(ለ) ስለሰውየው ማወቅ አልተቻለም (መ) ወሬው ድርግም አለ

15. ገርቡብ አለ

(ሀ) ጠጉብ አለ (ሐ) ፈዘዝ አለ

(ለ) ምቅ (መ) ጎደል አለ

16. የሥራ ደብዳቤ ሲፃፉ መጨረሻ ላይ መስፈር ያለበት የቱ ነው?

(ሀ) ዝርዝር ጉዳይ (ሐ) የተቀባይ አድራሻ

(ለ) የፀሀፊው አድራሻ (መ) የፀሀፊው ፊርማ

17. ለስራና ለወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ የጋራ ያልሆነው የቱ ነው?

(ሀ) ደብዳቤው የተፃፈበት ቀን (ሐ) የደብዳቤው ሀተታ ክፍል

(ለ) ደብዳቤው የተፃፈበት ቁጥር (መ) የደብዳቤው ማጠቃለያ ክፍል

18. ከሚከተሉት ውስጥ ‹‹-<u>ኣት</u>››የሚለውን ቅጥያ ምዕላድ የሚወስደው ቃል የቱ ነው?

(ሀ) ጥቁር (ሐ) ብልህ

(ለ) ደግ (መ) ምንጭ

19. ‹‹አስቴር የጠላውን አተላ ደፋችው።›› በሚለው ዐረፍተ-ነገር ውስጥ ያለው ‹‹-ን›› ተግባሩ ምንድን ነው?

(ሀ) ዘርፍ አመልካች (ሐ) ተሳቢ አመልካች

(ለ) ባለቤት አመልካች (መ) ጊዜ አመልካች

20. እሺም አላለቸኝ እምቢም አላለችኝ፣

አንድ ጠመዝማዛ ቆሎ ስቃ ዝም አለችኝ። ይህ ግጥም ከየትኛው አይነት ዘይቤ ይመደባል?

(ሀ) ተምሳሌት (ሐ) ተነጻጻሪ

(ለ) ተለዋጭ (መ) ሰውኛ

21. _____ማለት የአንድ ቃል ተደራቢ ፍች ነው።

(ሀ) ፍካሬያዊ (ሐ) መዝገበ ቃላት

(ለ) እማሬያዊ ፍቺ (መ) አገባባዊ ፍቺ

22. ቀጥተኛ ተሳቢ የሌለው አ.ነገር የትኛው ነው?

(ሀ) ቤቱ በጣም ሰፊ ነው (ሐ) ግንበኞቹ ህንፃውን አፈረሱት

(ለ) ህጻኑ ብርጭቆውን ሰበረው (መ) ወታደሮች አስፈሪውን አውሬ ገደሉት

23. ከሚከተሉት መዋቅሮች መካከል ግሳዊ ሀረግ የሆነው የትኛው ነው?

(ሀ) ክፉኛ ቆሰለ (ሐ) ከውሃው በላይ

(ለ) አዲስ ቤት (መ) ሰፊ እርሻ

24. ‹‹ሆዴ ላቀረበልኝ ጥያቄ ምንም ምላሽ አልሰጠሁትም።›› አረፍተ ነገሩ የቀረበበት የዘይቤ አይነት__ ነው።

(ሀ) ተለዋጭ (ሐ) ሰውኛ

(ለ) በስመሀዳሪ (መ) አያዎ

25. ‹‹ሽንጣ የንብ አውራ ነው።›› በሚለው ንግግር የተጠቀሰው ዘይቤ ምንድን ነው?

(ሀ) ተምሳሌት (ሐ) አነጻጻሪ

(ለ) ተለዋጭ (መ) ግነት

26. የልቦለድ አላባውያን ከሚባሉት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

(ሀ) ንግር (ሐ) መቼት

(ለ) ጭብጥ (መ) ንግር

27. ‹‹መቼም ሲሮጥ ኤሊ ነው የሚደርስበት የለም።›› ይህ ዘይቤ

(ሀ) ምፀት (ሐ) ግነት

(ለ) ሰውኛ (መ) እንቶኔ

መመሪያ ፫፦ የሚከተሉትን ልዩ ልዩ ጥያቄዎች እንደአጠያየቅ ባህርያቸው ተገቢውን መልስ ፃፍ/ፊ።

28. የስም ሙያ በመባል የሚታወቁትን የስም ተግባራት በሙሉ ዘርዝር/ ዘርዝሪ።

_____
_____
_____
_____
_____

29. አንድ ገፀ-ባህሪ ከሌሎች ፈንጠር ብሎ በመውጣትና ሌሎቹ እንዳልሰሙት በመቁጠር ሀሳቡን ለተመልካቹ የሚናገርበት ዘዴ_____ ይባላል።

30. ወደ አነስተኛ አሀድ ሊሸነሸን የማይችል የቋንቋ የመጨረሻ አሀድ_____ ይባላል።

31. በወጥ ገፀ ባህሪያት እና አስተነ ገፀ ባህሪያት መካከል ያለውን ልዩነት አብራራ/ሪ።

_____
_____ _____
_____
_____
_____
___

32. አምስት የኪነ-ጥበብ ዘርፎችን ፃፍ/ፊ።

ሀ. _____

ለ. _____

ሐ. _____

መ. _____

ሠ. _____

33. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አብራርተህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

1. ቃለተውኔት _____
2. ሴራ _____
3. ድንቃይ _____
4. ፀሀፊ-ተውኔት _____
5. ጎንታ _____
6. መራሔ ተውኔት _____

34. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች ለዪ/ ለይ። /የአንድ ድምፅ ስህተት ሙሉ ነጥብ ያስቀንሳል።/

ተ.ቁ	ቃል	ነፃ ምዕላድ	ጥገኛ ምዕላድ
1	ተማሪዎቻችን		
2	ልጆቹን		
3	መፃህፍት		
4	ተራራማነት		
5	ትዝታዎቻቸውን		

35. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በማንበብ የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ፃፍ/ፊ።

ሀ. ልጁ <u>በመኪና</u> መጣ።

ለ. <u>ክፉኛ</u> ታሚልሽ።

ሐ. በድንገት <u>ያዘው</u>።

መ. አንተ <u>ፈተና</u> የዛሬን ብቻ፤ ካሁን በኋላ ሳላጠና አልመጣም።

ሠ. እንደበግ <u>የዋህ</u> ነው።